የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Office of the Federal Auditor General

ቁጥር/Ref. No OFA[illegible]-F-04-23/1/16

ቀን/Date 08/07/2012

ለክቡር አቶ ዣንጥራር አባይ
የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ
አዲስ አበባ

ጉዳዩ ፤ የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል

ከላይ በርዕሱ የተጠቀሰው ኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 14 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 54 ገጽ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

መሰረት ዳምጤ
የኦዲት ዘርፍ ም/ዋና ኦዲተር

ግልባጭ፤

ለዋቸሞ ዩኒቨርስቲ
(68 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና
11 ገጽ የሂሳብ ሪፖርቶች)
ሆሳእና

ሣ.ቁ./P.O.Box- 457
አ.አ/Addis Ababa
ኢ/Ethiopia
ስልክ/Tel. +251115575701
+251115575550
+251115574057
+251115574500
ፋክስ/Fax +251115574468
ኢሜይል/E-mail- ofagit@ethionet.et
ድረገጽ/Website- www.ofag.gov.et
Office of the Federal Auditor General, Ethiopia

ቁጥር ዐ/ፌዋ·F.04.23/1/16
ቀን 30/03/2012

ለክብርት ወ/ሮ ፈትለወርቅ ገ/እግዚአብሔር

የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ ፣ <u>የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል፣</u>

ከላይ በርዕሱ የተጠቀሰው ኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 14 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 54 ገጽ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን ::

ከሰላምታ ጋር

መሰረት ዳምጤ
የኦዲት ዘርፍ ም/ዋና ኦዲተር

<u>ግልባጭ፣</u>

ለዋቸሞ ዩኒቨርስቲ

(68 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና

11 ገጽ የሂሳብ ሪፖርቶች)

<u>ሆሳእና፣</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ

የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል።

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል። ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና ሪፖርቶችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል።

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል:: የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል።

ሚኒስቴር ሪፖርት ማድረግ ሲገባው የወጪውንም ሆነ የገቢውን ሂሳብ ሪፖርት ያላደረገ በመሆኑ የተዘጋጀው የሂሳብ ሪፖርት የዩኒቨርስቲውን የተሟላ የሂሳብ እንቅስቃሴ እንዲያሳይ አድርጓል።

<u>የወጪ ሂሳብ፣</u>

3. ከሠራተኞች የተቀነሰ የሥራ ግብር ብር 22,961.40 በወጪና በገቢ ያልተመዘገበ በመሆኑ የዩኒቨርስቲው የገቢና ወጪ ሂሳብ በዚሁ መጠን ዝቅ እንዲል አድርጓል። ለመንግሥት ገቢ የሚደረገውን የሥራ ግብር መጠን እንዳይታወቅ ያደርገዋል።
4. የውሎ አበል ክፍያ ደንብና መመሪያን መሰረት በማድረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣
    - በዋና ግቢ በድምሩ ብር 94,586.00፣ በዱራሜ ካምፓስ ብር 65,715.00 እንዲሁም በህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 35,910.00 በአጠቃላይ ብር 196,211.00 የደመወዝ መጠን ሳይገለፅ የቀን ውሎ አበል የተከፈለ መሆኑ፣
    - በዋና ግቢ በድምሩ ብር 323,725.30 እና በዱራሜ ካምፓስ ብር 107,940.00 በአጠቃላይ ብር 431,665.30 የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ ቅጽ 1 ብቻ በመሙላት በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን፣
    - የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ ቅጽ 1 እና ማወራረጃ ቅጽ 2 ሳይሞሉ (ሁለቱምን ቅጾች ሳይጠቀሙ) በድምሩ ብር 727,858.00 ወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን፣

    በጠቅላላው ብር 1,355,734.30 የተከፈለውን ውሎ አበል ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም።

    በአጠቃላይ የውሎ አበል ደንብና መመሪያን ሳይከተል ብር 1,619,684.30 ተከፍሎ በመገኘቱ የተከፈለው ውሎ አበል የውሎ አበል አከፋፈልን መመሪያ የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም።
5. የውሎ አበል አከፋፈል በመመሪያው መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-
    - በድምሩ ብር 260,758.00 የውሎ አበል መመሪያ ሳይከተል ለመምህራን እና ሰራተኞች የምረቃ በዓል ላስተባበሩ በሚል የቀን ውሎ አበል የተከፈለ መሆኑን፣
    - በቀን 04/10/2011 በሒሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቀጥር 0006412 ለአቶ ሻምባ ሰይድ በተመሳሳይ ቀን ሁለት ጊዜ ብር 1,648.00 የተከፈላቸው መሆኑን፣

በሂሳብ መደብ 4211 ተመዝግቦ የተገኘ በመሆኑ ምዝገባውና ሠነዱ ታይቶ ተገቢው ማስተካከያ ቢደረግ፣

- በቀን 10/10/2011 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 0006419 ብር 45,337.00 ተከፍሎ ከተወራረደው ውስጥ የብር 23,879.00 የሰነድ ማስረጃ ሳይቀርብ ተወራርዶ የተመዘገበ መሆኑ፣
- በዋና ግቢ በድምሩ ብር 143,644.00 እና በዱራሜ ካምፓስ ብር 3,420.00 በአጠቃላይ ብር 147,064.00 ስልጠና ላይ መኖራቸውን (መሳተፋቸውን) የሚገልጽ የስልጠና ሰዓት መቆጣጠሪያ ሳይቀርብ የተከፈለ መሆኑ፣
- በዋና ግቢ በድምሩ ብር 1,499,510.55፣ በህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 65,797.01 እንዲሁም በዱራሜ ካምፓስ ብር 10,959.00 በድምሩ ብር 1,576,266.56 የዩኒቨርሲቲው ስልክ ቁጥር ወይም ኢንቴርኔት ቁጥር መሆኑ የሚያስረዳ ማስጃ ሳይቀርብ የተከፈለ መሆኑ፣
- ዱራሜ ካምፓስ በድምሩ ብር 217,333.89 የመነሻ ሰነድ ሳይኖር በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) ላይ በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፣
- በድምሩ ብር 708,018.69 ለምርምር ስራ እና ለኤሌክትሪክ ሽያጭ ክፍያ የወጣው ደጋፊ ሰነድ ሳይኖር በወጪ ተመዝቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፣

በጠቅላላው ብር 17,166,691.69 የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ በመሆኑ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም።

9. በተመሳሳይ ቀናት ከመደበኛ በደምሩ ብር 19,998.14 እና ከውስጥ ገቢ በድምሩ ብር 19,998.14 በድጋሚ በመከፈሉ የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ እና ወጪው እንዲንር አድርጓል።
10. ዩኒቨርሲቲ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በተፈቀደው መሰረት ክፍያ መፈጸም ሲገባው ያለምንም የክፍያ ተመን፡-
    - የዩኒቨርሲቲው መምህራን የሆኑ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ሲከታተሉ የነበሩ ትምህርታቸውን ከጨረሱበት ቀን ጀምሮ ወደ መደበኛ ሥራ መመለስ ሲገባቸው በኮንትራት (በጊዜያዊነት) ከዩኒቨርሲቲው ጋር ውል በመግባት፣ እንዲሁም ሌሎች ባለሙያዎች ቅጥሩ ሲከናወን ለሥራው ብቃት ያላቸው ስለመሆኑ የሚያስረዳ የትምህርት፣ የሙያና የሥራ ልምድ ማስረጃዎች ያላቀረቡ መሆኑ እና ክፍያውም በወር ለእያንዳዳቸው ከብር 51,646.00 እስከ ብር

በማለት ለኮሌጁ ኃላፊዎችና መምህራን እንደየኃለፊነታቸው በወር ብር 800.00 እና በወር ብር 1,000.00 መከፈሉንና በድምሩ ብር 539,801.60 በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የተከፈለ መሆኑን፣

በአጠቃላይ ብር 2,735,945.40 ያለአግባብ ለአኑዋላይዜሽን፣ ለኃላፊነት እና ለቤት አበል ተከፍሎ በመገኘቱ የመንግስትን ውስን ሀብት ለብክነት እንዲጋለጥ አድርጓል።

12.በሥራ አመራሩ ውሳኔ መሠረት በድምሩ ብር 2,002,920.00 የሀኪሞች የሥራ ጫና (overload) ተብሎ የተከፈለው የትርፍ ሰዓት ክፍያ መመሪያን ያልተከተለ በመሆኑ የመንግስትን ውስን ሀብት አለአግባብ ወጪ አድርጓል።

13.የጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት ካስተላለፈው መመሪያ ውጭ ለመምህራን በጠቅላላው ብር 1,267,836.26 ጥቅማ ጥቅም በመከፈሉ የህግ ጥሰትን ከማስከተሉ በተጨማሪ የመንግስት ውስን ሀብት አለአግባብ እንዲወጣ ተደርጓል።

14.ዩኒቨርስቲው ለተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም በበጋ ወራት ከሚሰጡ ትምህርትና ስልጠናዎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ብር 46,538.60 ከውስጥ ገቢ መከፈል ሲገባው ከመደበኛ በጀት ተከፍሎ በመገኘቱ ለመደበኛ ስራ የተመደበው በጀት ያለአግባብ ላልታለመለት ዓላማ እንዲውል ከማድረጉ በተጨማሪ የመደበኛው በጀት ሪፖርት ከፍ እንዲል አድርጓል።

15.በድምሩ ብር 1,455,823.61 በ2010 በጀት ዓመት ለተሰጠ አገልግሎት ከበጀት ዓመቱ ውጭ ተወራርዶ ተገኝቷል። በዚህ ምክንያት የሒሳብ ሪፖርቱ ላይ የተመለከተው ትክክለኛውን የበጀት ዓመቱን ወጪዎች እንዳያመለክት አድርጓል።

16.በአጠቃላይ ብር 1,510,466.67 ክፍያ ሲፈፀም ከወጪ ሰነዱ ጋር የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳይቀርብ ክፍያ ተፈጽሞ በመገኘቱ የወጪ ሂሣብን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም።

17.ዩኒቨርሲቲው የህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከመመሪያ ውጭ፣

- ለህክምና ባለሙያዎች ከወርሃዊ ደመወዛቸው በተጨማሪ የዶ/ሮች ማበረታቻ (ቶፕ አፕ) በማለት በወር ብር 10,000.00 እየታሰበላቸው ከውስጥ ገቢ ሂሳብ ላይ በድምሩ ብር 1,400,000.00 የተፈጸመ መሆኑን፣
- የማበረታቻ ክፍያ በማለት ለ3 ሰራተኞች ለእያንዳዳቸው ብር 2,000.00፣ ለ27 ሰራተኞች ለእያንዳዳቸው ብር 1,000.00 በድምሩ ብር 33,000.00 መከፈሉን፣

ተቀናሽ ያልተደረገና በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ ተመዝግቦ ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ፣

- ከዋና ግቢ ብር 38,045.26 እና ዱራሜ ካምፓስ ብር 68,536.59 ተቀናሽ ያልተደረገ እና ያልተመዘገበ የተጨማሪ እሴት ታክስ መገኘቱ፣

በጠቅላላው ብር 203,637.30 የቅድመ ክፍያ ግብር፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የመያዣ ሂሳብ ተቀንሶ በሪፖርት ባለመካተቱ መንግስት የሚያገኘውን ገቢ እንዲያጣ አድርጓል።

21.የውሃ ፍጆታ፣ የስልክ አጠቃቀም እና የመብራት ወጪ በዩኒቨርሲቲው የሚታወቁ የውል ቁጥሮች ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 38,990.83 የነሐሴ፣ ሐምሌ እና የመስከረም ወር የውሃ ፍጆታ ተብሎ የተከፈለው ከቀረበው የዩኒቨርሲቲው ውል ቁጥር ውጭ በሆኑት በቁጥር 60172 ብር 38,245.57 እና በቁጥር 60210 ብር 745.26 በመክፈሉ በአጠቃላይ ብር 38,990.83 አለአግባብ ዩኒቨርስቲው ላልተዋዋላቸው የውል ቁጥሮች ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣
- ምንም ዓይነት የውሃ የውል ቁጥር ሳይጠቀስ ብር 153,650.00 ክፍያው ለዩኒቨርሲቲው የውሃ ፍጆታ የተከፈለ ስመሆኑ ማረጋጋጥ አለመቻሉን፣
- በዱራሜ ካምፓስ ለኤሌክትሪክ አገልግሎት የተከፈለው የመብራት ፍጆታ በድምሩ ብር 215,163.16 ለኦዲት ከቀረበው የዩኒቨርስቲው ውል ቁጥር ውጭ መሆኑን፣
- የዩኒቨርሲቲው የስልክ ቁጥር፣ የሞባይል ቁጥር እና የፋክስ ቁጥር ዝርዝር ውስጥ ለሌሉ ቁጥሮች በድምሩ ብር 34,971.71 ተከፍሎ መገኘቱን፣
- ወደ ውጭ ሀገር አጭር መልዕክትም ሆነ በድምፅ መልዕክት ማስተላለፍ ያልተፈቀደላቸው የተለያዩ የሥራ ክፍሎች አጭር መልዕክትና የድምፅ መልዕክት በማስተላለፍ በድምሩ ብር 6,736.86 ተከፍሎ መገኘቱን፣

በጥቅሉ ብር 449,512.56 ዩኒቨርስቲው ካቀረባቸው ዝርዝር መረጃዎች መሠረት ባለመሆኑ ያለአግባብ የተከፈለ እና የአገልግሎት ክፍያው ለዩኒቨርስቲው አገልግሎት ስለመዋሉ ማረጋገጥ አለመቻሉን።

22.ዩኒቨርሲቲው የተለያዩ አገልግሎት ግዥዎችን በዘርፉ የተሰማሩትን በማወዳደር በዝቅተኛ ዋጋ አገልግሎቱን ማግኘት ሲገባው ያለ ምንም ውድድር በቀጥታ ግዥውን

በመጨመር በድምሩ ብር 3,000.00 ተከፈሎ ተመዝግቦ ሪፖርት በመሆኑ አለአግባብ የዩኒቨርስቲው ወጪ ከፍ እንዲል አድርጓል፡፡

28. ብር 16,510.00 ለነዳጅ ግዥ ቅድሚያ ክፍያ የወጣ በተሰብሳቢ ሂሳብ ተመዝግቦ ሪፖርት መደረግ ሲገባው በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) ላይ በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ በመሆኑ የተሰብሳቢ ሂሳብ ዝቅ እንዲል እና የወጪ ሂሳ ደግሞ ከፍ ተደርጎ ሪፖርት በመደረጉ የተሰብሳቢ እና የወጪ ሂሳብ ትክክለኛ ሚዛን እንዳያሳይ አድርጓል፡፡

29. የመኪና ሰርቪስ አገልግሎት ግዥ ከአግታ ኃ/የተ የግል ማህበር የፈፀመ ሲሆን፣ ለድርጅቱ የተከፈለው ገንዘብ ብር 141,392.66 መሆኑን በገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ቁጥር CA 00002027 የተረጋገጠ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው በቀን 05/03/2011 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 55613 ብር 121,512.26 ብቻ በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት ስለተደረገ በልዩነት ብር 19,880.40 በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት ያልተደረገ በመሆኑ የተዘጋጀው የወጪ ሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገጽታውን እንዳያሳይ አድርጓል፡፡

<u>የተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

30. በ2011 በጀት ዓመት መጨረሻ የተሰብሳቢ ሂሳብ በድምሩ ብር 204,705,465.11 የሚታይ ቢሆንም ተቀጽላ ቋት ያልተከፈተላቸው በመሆኑ በተሰብሳቢ ሂሳብ የተያዘበት ጊዜ እና ገንዘቡ ከማን እንደሚፈለግ በቀላሉ ለማግኘት ያልተቻለ በመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግና በወቅቱ ለመሰብሰቡ ባለመታወቁ የተሰብሳቢውን ሂሳብ በእርግጥ እውነተኛ ተሰብሳቢ መሆኑን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

31. የውስጥ ገቢ ተሰብሳቢ ሂሳብ የሂሳብ መደብ 4211 ብር 495,237.13 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (መደበኛ ባልሆነ ሚዛን) በክሬዲት የሚታይ በመሆኑ የተሰብሳቢው ሂሳብ በዚሁ መጠን ዝቅ እንዲል የሚያደርግ በመሆኑ ሂሳቡ ተጣርቶ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

<u>የተከፋይ ሂሳብ፣</u>

32. በ2011 የተከፋይ ሂሳብ በድምሩ ብር 143,331,260.59 የሚታይ ቢሆንም ተቀጽላ ቋት ያልተከፈተላቸው በመሆኑ በተከፋይ ሂሳብ የተያዘበት ጊዜ እና ገንዘቡ ለማን እንደሚከፈል በቀላሉ ለማግኘት ያልተቻለ በመሆኑ የተከፋዩን ሂሳብ በእርግጥ እውነተኛ ተከፋይ መሆኑን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ድምር በማነስ ሪፖርት የተደረገ በመሆኑ ሪፖርቱ ትክክለኛ ገፅታ እንዳያሳይ አድርጓል።

- የተሰብሳቢ ሂሳብ የተጠቃለለ ሂሳብ ሪፖርት በድምሩ በብር 23,665.57 በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ ከተመዘገበው የሶስቱ ግቢ ድምር በማነስ ሪፖርት የተደረገ በመሆኑ ሪፖርቱ ትክክለኛ ገፅታ እንዳያሳይ አድርጓል።
- የተከፋይ ሂሳብ የተጠቃለለ ሂሳብ ሪፖርት በድምሩ በብር 13,013,806.14 በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ ከተመዘገበው የሶስቱ ግቢ ድምር በማነስ ሪፖርት የተደረገ ሲሆን፣ በሂሳብ መደብ 5061 ብር 32,177.70 በመብለጥ ሪፖርት የተደረገ በመሆኑን ሪፖርቱ ትክክለኛ ገፅታ እንዳያሳይ አድርጓል።
- የወጪ ሂሳብ በተለያዩ ሂሳብ መደቦች የተጠቃለለ ሂሳብ ሪፖርት በድምሩ በብር 60,581,648.03 በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ ከተመዘገበዉ የሶስቱ ግቢ ድምር በመብለጥ ሪፖርት የተደረገ ሲሆን፣ በተወሰኑ ሂሳብ መደቦች በድምሩ ብር 58,773,346.11 የተጠቃለለ ሂሳብ ሪፖርት በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ ከተመዘገበው የሶስቱ ግቢ ድምር በማነስ ሪፖርት የተደረገ በመሆኑ ሪፖርቱ ትክክለኛ ገፅታ እንዳያሳይ አድርጓል።

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 36 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ የሆኑ ምክንያቶች በእኛ አስተያየት የዩኒቨርስቲውን የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት ያሳያሉ በማለት አስተያየት መስጠት አልተቻለም።

<u>ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች</u>

ምንም እንኳን በሰጠነው አስተያየት ላይ ለውጥ ባያስከትሉም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል።

- በተገባው ውል ውስጥ የውል የማስከቢሪያ ጊዜ ያልተቀመጠ በመሆኑ በቀረዉ የውሉ መጠን ላይ የጉዳት ካሳ ማስላት ያልተቻለ መሆኑን፣
- ለምርምር ኮንፈረንስ ህትመት ስራ ለብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት የቅድሚያ ክፍያ ተብሎ የጠቀላላ ውሉ ዋጋ ብር 236,560.75 ውስጥ 30% ብር 70,968.23 መስጠት ሲገባው፣ የውሉን ዋጋ 50% ብር 118,280.37 በመክፈሉ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ

የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች

መግቢያ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርሲቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

የሪፖርቱ ዓላማ፣

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፣

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፣

- የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ ሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን፣ ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

ለገንዘብ ሚኒስቴር የተላኩ የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ በሚሰጥና መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::